የሰ/መ/ቁ. 79105
ሐምሌ 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ - ጠበቃ ሜላት ወርቅ ኃይሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መዘምር መክብብ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርጎ የቀረበውን የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት ሲታይም ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ግንኙነት ያለጥፋት የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በድርጅቱ ግቢ ውስጥ ድብደባ ፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና የጠብ አጫሪነት ተግባር በመፈፀማቸው ስለመሆኑ ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በሁዋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በአመልካች ኤዲፒ ካምፕ እና ለሰራተኞች መኖሪያነት በተሰራው ግቢ ውስጥ /በስራ ቦታ/ የድርጅቱን ሰራተኛ በመደብደብና የዛቻ ተግባር መፈፀማቸው መረጋገጡንና ለዚህም ተጠያቂ መሆናቸውን ገልፆ የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ወሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ተጠሪ የድብደባ ተግባሩን የፈፀሙት ከስራ ሰዓት ውጪ በመሆኑ ድርጊቱ በስራ ቦታ ላይ እንደደረሰ የሚቆጠር አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካች ለተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ለስራ ስንብቱ ምክንያት የሆነውን የድብደባ ተግባር ስለመፈፀማቸው ከመረጋገጡም በላይ ድርጊቱ የተፈፀመው በስራ ቦታ ላይ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ድርጊቱ ከስራ ሰዓት ውጪ የተፈፀመ ተግባር ነው በሚል ጠባብ ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ

የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና አግባብነት ያለውን ሕግ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው ተጠሪ አምባጓሮ ፈጥሮ የስራ ባልደረባውን መደብደቡን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀብሎ ድብደባው የተፈፀመው ተጠሪና የግል ተበዳይ አመልካች ባዘጋጀላቸው የስራና የመኖሪያ ግቢ ካምፕ ቢሆንም ድብደባው የተከናወነው ከስራ ሰዓት ውጪና በመፀዳጃ ቤት አካባቢ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ረ)) ስር የተደነገገውን አያሟላም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውድቅ ማድረጉና ወደ ስራው ይመልሰው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት በሚል ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪው የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ላይ የስራ ቦታ በሆነው የአመልካች ካምፕ እና በስራ ጉዞ ላይ የድብደባ ፣ የዛቻ ተግባር መፈጸማቸውን ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑንና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቢሆን የድብደባውና የዛቻው ተግባር በተጠሪ በመፈፀሙ ረገድ ከስር ፍርድ ቤት የተለየ ድምዳሜ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክርም ተጠሪ የድብደባውን ተግባር ስለመፈፀማቸው ግልፅ የሆነ የክህደት ክርክር የሌላቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የተጠሪ ድርጊት የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ የተደነገገውን ጥፋት አያሟላም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የአመልካች ሰራተኛ የተደበደበችው ማታ ከመሆኑም በላይ የድብደባው ተግባር የተፈጸመው አመልካች ለሰራተኞቹ በመኖሪያነት ባዘጋጀው ቦታ መጸዳጃው አከባቢ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በሕጉ አነጋገር የስራ ቦታ እና ሰአት የሚለውን መለኪያ የሚሸፈን አይደለም በሚል ነው፡፡ አመልካች ሰዓቱም ሆነ ቦታው የስራ ቦታ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜን ተገቢነት ለመመርመር የተጠቃሹን ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ በዝርዝር መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ረ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ፡- “ እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባጓሮ ወይም ጠብ እጫሪነት ተጠያቂ መሆን ” ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ ከሚያስችሉ ምክንያቶች አንዱ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሐረግ "….በስራው ቦታ…." የሚለው ሲሆን ይኸው ሐረግ ሰራተኛው ስራውን በስራ ሰዓት የሚያከናውንበትን ቦታ ወይም የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ ሊያውል የተገኘበትን ቦታ ሁሉ የሚያጠቃልል ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 97 እና 4 ድንጋጌዎችን ይዘት በማገናዘብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አሰሪው ስራው በሚሰራበት ካምፕ ውስጥ ለሰራተኛው በመኖሪያነት የመደበውን ቦታ እና በዚህ ቦታ ሠራተኛው ያለበትን ሠዓት ጭምር ሁሉ ሊጠቃልል እንደሚችል ከሕጉ መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ሰራተኛው በስራ ሰዓት ስራውን በሚያከናውንበት ቦታ ወይም የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ ሊያውል በተገኘበት ቦታ ላይ እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባጓሮ ወይም ጠብ እጫሪነት ድርጊት መፈፀሙ ከተረጋገጠበት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ድርጊት ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ አይነተኛ አላማም በሥራ ቦታ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ምርትና

ምርታማነትን ለማሳደግ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ሊተረጎም የሚገባውም ይህንኑ የድንጋጌውን ዓላማ መሰረት በማድረግ ሊሆን እንደሚገባም እሙን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን ሰራተኛ መደብደቡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠና በተጠሪም የታመነ ፍሬ ነገር መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ይህ የተጠሪው ድርጊት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ የጠብ አጫሪነት ድርጊት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ፍ/ቤት ተጠሪው የድብደባውን ድርጊት መፈፀማቸውን ተቀብሎ ድርጊቱ የተፈጸመው ከስራ ሰዓት ወጪ ነው በማለት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠውና ከሕጉ መንፈስና አላማ ውጪ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ የአሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው ትእዛዝ በማክበር ካምፑ በሚገኝበት ቦታ መኖሪያ ተሰጥቶት በመኖር ላይ ባለበት ሁኔታ በዚሁ አካባቢ በድርጅቱ ሰራተኛ ድብደባ ከተፈፀመበት የድብደባውን ተግባር የፈፀመው ሰራተኛ ተግባሩን የፈፀመው በስራ ጊዜና ቦታ አይደለም ተብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ሕጉ ሊያሳካ ያሰበውን ፤ በስራ አካባቢ ሰላምን በማስፈን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የሚለውን አላማ ያላገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የድብደባውን ተግባር የፈፀሙ ስለመሆኑና ድብደባውን የፈፀሙትም ለስራ ጉዳይ ከተጠሪ ጋር እንዲሄዱ በአመልካች የታዘዙትን ሴት ሰራተኛ ቀኑን ሙሉ ሲያስቸግሯቸው ውለው አሰሪው በስራው ቦታ ውስጥ ባዘጋጀው የሠራተኞች መኖሪያ ቤት መፀደጃ ቤት ሰራተኛዋ ቆይተው ሲወጡ ማታ ላይ መሆኑ የተጠሪን ድርጊት ጥፋት ከባድነት አመልካች ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪው ድርጊት የአዋጁን አንቀጽ 27/1/ረ የተመለከተውን ጥፋት አያሟላም ሲል የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጉ ያስቀመጠውን የሰራተኛውን ግዴታ የሚመለከተውን ድንጋጌ እና የጥፋቱን አደገኛነት ከተጠቃሹ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ አንፃር በአግባቡ ሳያገናዝብ መሆኑን ስለተረዳን ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 116083 ሚያዚያ 08 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 74140 ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ